# ዋሺንግተን ዲሲ የእሳት እና የድንገተኛ ሕክምና አገልግሎቶች መምሪያ

## የእሳት ማርሻል ጽሕፈት-ቤት – ጠቅላይ እዝ

| | |
|---|---|
| **ርእሰ-ጉዳይ: የስብሰባ ፈቃዶች** | **ጠቅላይ እዝ:** 617 |
| **ክፍል:** እቅዶች እና ፈቃዶች | **የወጣበት ቀን:** ጥቅምት 1, 2009 |
| **ባለስልጣን:** DCMR 12, ምዕራፍ 12H, ክፍል F-107H<br>የእሳት መከላከያ ኮድ ደጋፊ | **አገልግሎት የሚያበቃበት ቀን:** እስከ ሚወገድ ድረስ |

**I. አድማስ**

በዚህ ሰነድ ውስጥ የሚገኘው መረጃ ለሁሉም ከዲሲ እሳት እና ድንገተኛ ሕክምና አገልግሎቶች መምሪያ የእሳት መከላከል ክፍል የህዝባዊ ስብሰባ ፈቃድ ለማግኘት የሚጠይቁ አመልካቾች ያገለግላል።

**II. አላማ**

የዚህ ጠቅላይ እዝ አላማ የስብሰባ ቦታ እና የፍጻሜዎች ማከናወኛ ፈቃድ ጥያቄዎች አቀባበል እና ክንውን ሂደት ደረጃው የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ነው።

**III. የቃላት ፍች**

የለም

**IV. ፖሊሲ**

በአንድ በኩል የስብሰባ ቦታዎች እና ፍጻሜዎች ማከናወኛ ፈቃዶች ጥያቄዎች ጉዳይ ብቁ እና ስርአት ባለው አካሄድ እንዲሁም ያለምንም መዘግየት ማከናወን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የህብረተሰቡን፣ የአከናዋኞችን፣ እና የተቆጣጣሪዎችን ደህንነት ማረጋገጥ እንዲሁም ህጎችን፣ ደንቦችን እና ስነስርአቶችን አክብሮ መስራት የእሳት ማርሻል ጽሕፈት-ቤት ፖሊሲ ነው።

**V. አሰራር**

የመሰባሰብ ፈቃድ ጥያቄዎች የሚመጡት በተለያየ መልኩ ነው፣ ስለዚህ ከሌሎች አዳራሹ ላይ የሚካሄዱ የተፈቀዱ እንቅስቃሴዎች (ለምሳሌ፣ ፓይሮቴክኒክስ) ነጥሎ ለየብቻ መገምገም ሊያስፈልግ ይችላል። አዳራሾቹ የስብሰባ ቦታ ሆነው ለማገልገልም ፈቃድ ሊኖራቸው ይገባል።

*ሀ.* **<u>አውደርእይ፣ ስብሰባዎች እና የንግድ ትርኢቶች</u> (IFC ምዕራፍ 3 እና 10)**

1. ሁሉም የተሞሉ የፈቃድ ማመልከቻዎች እና ለዲሲ ግምጃቤት ተከፋይ የሚሆኑ ትክክለኛ መጠን የያዙ የቼክ ወይንም የገንዘብ ትእዛዞች ወደ የእሳት ማርሻል ጽሕፈት-ቤት በአካል በመሄድ ማስረከብ የግድ ይላል። (ማስታወሻ: ማመልከቻው በእሳት ማርሻል ጽሕፈት-ቤት እና ኦንላይን ላይ ይገኛል)። እቅዶች ፍጻሜው ከሚጀምርበት ጊዜ ቢያንስ ከ 10 የስራ ቀናቶች በፊት ከገምጋሚው እጅ መግባት አለባቸው።

2. ክንዋኔው በሚገባ ፈቃድ ማግኘቱን የሚያሳዩ ሰነዶች (DCRA, ወይንም ሌላ ፈቃድ ሰጪ ተቋም)።

3. አንድ እቅድ የሚከተሉትን ማካተት አለበት:
   ሀ. የባለጉዳዩ አድራሻ ያለበት እና ማህተም የተደረገበት ፖስታ (መጠኑ በቂ መሆን አለበት)።
   ለ. የሁሉም መውጪያ በሮች መገኛ ቦታ እቅዶቹ ላይ መታየት አለበት።
   ሐ. የሁልም መውጪያ ኮሪደሮች እና መተላለፊያዎች አቅጣጫዎች።
   መ. የቦታውን ስፋት ጨምሮ ሁሉም አስፈላጊ የቦታው መረጃዎች።

4. እቅዶቹ የባለጉዳዩ አድራሻ ያለበት እና ማህተም የተደረገበት ፖስታ (መጠኑ በቂ መሆን አለበት) አጠቃለው እንዲይዙ ከተደረጉ መመለስ ይቻላል።

5. አስፈላጊ ሲሆን፣ አጥጋቢ የቦታ ፍተሻ ከተደረገ በኋላ ፈቃዶች ይሰጣሉ።

## ለ. <u>ኮንሰርቶች</u> (IFC ምዕራፍ 3 እና 10)

1. ሁሉም የተሞሉ የፈቃድ ማመልከቻዎች እና ለዲሲ ግምጃቤት ተከፋይ የሚሆኑ ትክክለኛ መጠን የያዙ የቼክ ወይንም የገንዘብ ትእዛዞች ወደ የእሳት ማርሻል ጽሕፈት-ቤት በአካል በመሄድ ማስረከብ የግድ ይላል። (ማስታወሻ: ማመልከቻው በእሳት ማርሻል ጽሕፈት-ቤት እና ኦንላይን ላይ ይገኛል)። እቅዶች ፍጻሜው ከሚጀመርበት ጊዜ ቢያንስ ከ 10 የስራ ቀናቶች በፊት ገምጋሚው እጅ መግባት አለባቸው።

2. ክንዋኔው በሚገባ ፈቃድ ማግኘቱ የሚያሳዩ ሰነዶች (DCRA, ወይንም ሌላ ፈቃድ ሰጪ ተቋም)።

3. አንድ እቅድ የሚከተሉትን ማካተት አለበት:
   ሀ. በግልፅ የሚታይ ዝርዝር የፎቁ ካርታ።
   ለ. የሁሉም መውጪያ በሮች መገኛ ቦታ እቅዶቹ ላይ መታየት አለበት።
   ሐ. የሁልም መውጪያ ኮሪደሮች እና መተላለፊያዎች አቅጣጫዎች።
   መ. የቦታውን ስፋት ጨምሮ ሁሉም አስፈላጊ የቦታው መረጃዎች።

4. እቅዶቹ የባለጉዳዩ አድራሻ ያለበት እና ማህተም የተደረገበት ፖስታ (መጠኑ በቂ መሆን አለበት) አጠቃለው እንዲይዙ ከተደረጉ መመለስ ይቻላል።

5. አስፈላጊ ሲሆን፣ አጥጋቢ የቦታ ፍተሻ ከተደረገ በኋላ ፈቃዶች ይሰጣሉ።

ማስታወሻ: ፎቅ ላይ የሚደረግ የህዝብ ስብሰባ ፈቃዶች በተመለከተ የሚነሱ ሁሉም ጥያቄዎች ወደሚከተለው መላክ አለባቸው:

**District of Columbia**
**Fire & Emergency Medical Services Department**
**Fire Prevention Division**
**1100 4th Street SW Suite E700**
**Washington, DC 20024**
**(202) 727-1600**